# ያኔ!

መርሳትስ ብጀምር አርጅቼ ጃጅቼ
አንድ ዘፈን ባስታውስ ሌሎቹን ረስቼ
በተሰበረ ድምፅ ያንን ባንጎራጉር
ነግቶ እስኪመሽም እእ... ህህ... ምም...ስል ብውል

ዓተርን መቆርጠም አጥንትም ቢያቅተኝ
እንድያው ይባስ ብሎ መብላት ቢታክተኝ
ጥርሴ ሁሉ ወልቆ ድዴም ቢሻግት
ጉልብቴ ተዳክሞ ወኔዬም ቢሞት
አፌ ተቆላልፎ መናገርም ባልችል
"እፍ" "እስ" ቢያሰኘኝ "ፕ" እላለሁኝ ስል

ደክሞና ደብዝዞ አላይ ሲለኝ ዓይኔ
ደጋፊና መሪ ስፈልግ ከጎኔ
"አይዞህ፣ አለሁልህ!" ትይኛለሽ ያኔ?

አልራመድ ሲለኝ እግሬም ለግሞ
አጎንብሼ ስሄድ ወገቤ ተጣሞ
ሳዘግም ስጎተት ምርኩዝ ብጤ ይገፍ
ትወጂኝ ይሆን ወይ ያን ጊዜ፣ ያን ጊዜ!

ቢጸናብኝና ጆሮየም ባይሰማ
ነገር ብቀላቅል ከሰው ባልስማማ
ቁጣ ቁጣ ቢለኝ ቢወጣኝ ኃይለ ቃል
ያኔ...ያኔ... ፍቅርሽ ያልቃል?
ለኔስ ያለሽ ስሜት ያበቃል?
ወይስ ከዛም አልፎ ይዘልቃል?

ካሳ በ. በላይ